# ትግራይም አላሸነፈን፣ ነፃም አያወጣን
# (ምነዋ መገዛቱና መዋረዱ ቢያብቃ!)

ከመላኩ ይስማው

በቅርቡ አንድ ራሱን ዣንጥራር ተክሌ ከቫንኩቨር ብሎ የጠራ ግለሰብ ለቀድሞ ወያኔዎች በተለይም አረጋሽ አዳነን ለመደገፍ ብሎ በጻፈው ጽሁፍ የተሸነፍነውም፣ የምንድነውም በትግራይ ነው የሚል አሳዛኝ መልዕክት ማስተላለፉን በንዴት ማንበብ ተገደናልና በዝምታ ማለፉ ደግ አልመሰለኝም። የናት ሆድ ዥንጉርጉር ነውና ነገሩ፣ አሳፋሪ ዜጎች ሞልተዋል።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ስርየት ሆነ ነፃነት ከመለስ የተጣሉ ግን ወያኔነትን ዛሬም በፍቅር አቅፈው ካሉ ጥቂቶች የሚገኝ አለመሆኑን መረዳት የተሳናቸው፣ ነገር ዓለሙ የተምታታባቸው ወይም መለስን ቢጠሉም የትግሬዎችን የበላይነት ግን ሽኮሪና ባዮች /አፍቃሪዎች/ ብቻ ናችው ይህን የሚሉን። ስዬን ሆነ አረጋሽን ሃገር አዳኝ ብሎ ለመቀብል ሩጫው ውርደትና ቅሌት አዘል መሆኑ አልቀረምና አቶ ተክሌ ተብዬው ሆነ ግለሰቦቹን በየመድረኩ የሚያስተናግዱት ሁሉ መጋለጣቸው አልቀረም። በትግራይ ተሸነፍን የሚሉን ለዚህ ነው። ኢትዮጵያም ሆነች ሕዝቧ በትግራይ አልተሸነፈም። ደርግም ቢሆን ወያኔ እንደሚለው በ "ልዩ ጀግኖች" የትግራይ ልጆች የተሸነፈ ሳይሆን በኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ነው የተሸነፈው። የተክሌ ድምዳሜ ወያኔ ወያኔ ትሸታለች። በሌላ በኩል ደግም ይህን ዓይነት ድምዳሜ የሚመጣው ተስፋቸውን የቆረጡ፣ ለወያኔ እጅ የሰጡ፣ የተጎነበሱ፣ ሕዝብ የካዱ፣ እውነትም የትግራይ ተወላጆች ብቻ ናቸው ጀግኖችና ጦርነት ሰሪዎች ብለው ከሚያምኑ ምስኪኖች ናቸው። ወያኔና ሻዕቢያ ስልጣን እንደያዙ ሰሞን፣ ሌላውን ተስፋ ለማስቆረጥ፣ ከሰውም በላይ ሰው ፈጣሪ ነን ሲሉና የነበረውን የሕዝብ እንቅስቃሴ ሁሉ እኛ መራነው ብለው ሲመጻደቁና የሌላውን ወኔ ለመስለብ ሲሞክሩ ታዝበን ነበር። በዚያን ጊዜ ሰለባ የሆኑና እነ ወያኔ አይቻልም ብለው የተደፉ ጥቂቶች አልነበሩም። የተክሌ እነሱ አሸነፉን እነሱው ያድኑን አሳፋሪ ጫጫታ የዚሁ ነጸብራቅ ነው።

በተደጋጋሚ በሃገር ወዳዶች ሲነገር እንደቆየው ትግራይንም ጨምሮ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ የሚገላገለው በጋራ ትግሉ እንጂ በትግራይ ነፃ አውጪዎች አይደለም - ሊሆንም አይችልም። እነ ስዬና አረጋሽ ወይም ገብሩ አስራት ካልታገሉልን ነፃ

መውጣት የማንችል ከሆነማ፣ ሃገራችንን ማዳን የማንችል ከሆነማ፣ ነፃ ባንወጣ ቢቀር ይሻላል። የተክሌና መሰሎቹ ሰበካ ወያኔ ካልሆኑ በስተቀር በጣም አሳፋሪና አዋራጅ ነው። ወያኔ ከሆኑ ግን እንረዳላቸዋለን -- ትምክህታችው አስቸግሯቸው ነውና።

ባለፈው አንድ ጽሑፌ እንዳልኩት <u>ሞኝን እባብ ሁሉት ጊዜ ይነክሰዋል አሉ። መጀመሪያ ሳያየው፣ ሁለተኛው የነከሰውን (እባቡን) ለሌላው ሰው ሲያሳይ።</u> ስልጣን ላይ ያለውን የወያኔ ቡድን በሳልሳዊው (በሶስተኛው) ወያኔ ማለትም በአረና ትግራይ ቡድን አባላት እንተካ ምክርም የዚሁ ቢጤ ነው። ትላንት በመለስ መሪነት፣ በስዬ ጦር አዛዥነት፣ በነአረጋሽ፣ ገብሩ አስራትና ሌሎችም ጥምረት ጥረት ብዙ ብዙ ብሔራዊም ግለሰባዊም ግፎች፣ ወንጀሎች ተፈፀሙ። የምክትል ሚኒስተርነት፣ ኮሚሽነርነት፣ ወዘተ ትንንሽ የስልጣን ትርፍራፊ እየተቀበሉ የሸጡንን ሆዳሞች ሳንረሳ ማለት ነው። ታዲያ ዛሬ የወያኔው ቡድን እርስ በርስ ስለተጣላ ብቻ፣ ለእነኝሁ ወንጀለኞች ዕጣ ፈንታችንን እንሰጥ ዘንድ እነተክሌና መሰሎቹ ሊሰብኩን ይሻሉ። ጭራሽም ቀኝ እጅ ሆነን እነሱ ሌላ ዙር እንዲገዙን እንረዳቸው ዘንድ ደፍረው እስከመስበክ ደርሰዋል። ታላቁ ፀሐፊ ሐማ ቱማ እንዳሉት «ታሪኩን የረሳ፣ ካባቱ ገዳይ ይተኛል» እንዲሉ ቢጤ እንሆን ዘንድ ይጠይቁናል። ትላንት የመለስና የአረናው ቡድን አባላት አብረው ያረቀቁት ሐገርን በታኝ፣ ያንድ ቡድን መርሐ-ግብር በሕገ-መንግስትነት እንደተጫነብን፣ በእነኝሁ ወንጀለኞች የተከፈቱት የትግራይና የሌሎችም የዋሻ እስር ቤቶች በር እንደተከረቸመ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት ታሳሪዎቻቸው የእጅ የእግራቸው ሰንሰለት ሳይወልቅላቸው፣ የታፈኑት የተገደሉት ሰማዕታት ጥሪ የፍትህ ምላሽ ሳያገኝ የነመለስን ወያኔ በነገብሩ አስራት (ሳልሳዊ) ወያኔ ተክተን ለመገዛት እንዘጋጅ፣ ከመዘጋጀትም አልፎ እንተባበር ዘንድ ነው የሚሰብኩን።

ከአረጋዊ በርሄ እስከ አረጋሽ አዳነ፣ ሁሉም ከመለስ ተጣላን ባዮች እስካሁን ስለወያኔ ያሉንን ወይም ያደረጉትን ልብ ብላችሁ አስቡት እስኪ። እንደታዘብኩት የወያኔ አመራሮች ይጣሉም፣ ይተሳሰሩም፣ ሌላው ቀርቶ ይገዳደሉ ዝንፍ የማይሉባቸው ሁለት የጋራ ፀባይ አላቸው።

አንዱ ምስጢራቸውን መጠበቃቸው ነው። በደም ተወልደው፣ በደም ያደጉ፣ በደም የሚኖሩ ወንጀለኞች ቢሆኑም አብረው እያሉ ስለተፈፀመ ወንጀል ትንፍሽ አይሉም - ከአቶ ገብረመድህን አርአያ በቀር። ስለወያኔና ስለፈፀመው ወንጀል የሚነግሩን

እየቆጠቡ ነው። ብዙ ጊዜም ሃገር ያወቀውን፣ ፀሐይ የሞቀውን። ሰሞኑን እንኳ ስዬ አብርሃ እ. ኤ. አ. በ1984 የተሰጠው ዕርዳታ ለመሳሪያ መግዣነት ስለመዋሉ ሲጠየቅ በሰጠው መልስ - አትግፉን! አለበለዚያ ብዙ ጉድ አለ የማወጣው! ማለቱ የዚሁ ቃል ኪዳናቸው ምስክር ይመስለኛል። ሌላው ፀባያቸው ደግሞ ከተጠናወታቸው የታላቋ ትግራይ ትግሪኝ ቅዠት እና የእነሱን ቡድን በበላይነት የማቆየት ስልት መቆራኘታቸው ነው። ከዘር ፖለቲካ አረንቋ ውስጥ ላይለያዩ ተማምለዋል። ለዚህም ነው ካመታት በሁዋላም ሌላውን የወያኔ ቡድን በአረና ትግራይነት ሰይመው ብቅ ያሉት።

የተቃዋሚው ጎራም ጽናት በሚጎላቸው፣ አቋምን እንደሸሚዝ በሚቀያይሩ ቴአትረኞች ስለተሞላ ይኸው ትላንትም (ስልጣን ላይ ባለው ወያኔ) ዛሬም (በሳልሳዊ ወያኔ ማለትም በአረና ትግራይ በኩል) የወያኔ መሪዎች የሆኑት የሚስተናገዱበት ሆኗል። ከሚሰሩብን ይልቅ የሚያወሩልንን፣ በእውን ከሚያስኖሩን ይልቅ የሚያስቃዡንን የምናምን ከመሆኑ አባዜ መላቀቅ አለብን። ሁለቱም፣ እነመለስም ሆኑ የአረና ትግራይ ወያኔዎች ከስልጣን ጠብ በስተቀር የአቋም ልዩነት የላቸውም። ያፈጠጠው ሃቅ ይህ ነው። ትላንት ከአስመራ ላይ ቁጭ ብለው የኤርትራን የባርነት ወይስ ነፃነት ትመርጣለህ የቀልድ ሪፈረንደም እያዳነቁ ለወያኔ ጋዜጣ ይዘግቡ የነበሩ ተከታዮቻቸው ዛሬ በድረ-ገፃቸው ሊያሰማምሯቸው ቢሞክሩም።

በሌላ በኩል ግን ትላንትም ዛሬም በጽናት ጸረ-ኢትዮጵያ፣ ጸረ-ህዝብ የሆነውን ወያኔያዊ አቋም የታገሉ፣ የሚታገሉ ብዙ ጀግኖች አሉን። ከጭፍን ስሜታዊነት እና ጥላቻ የራቀ ማመዛዘንን ቢጠይቅም ከጽኑ አቋማቸው ዝንፍ ያላሉ፣ እንደማይሉም ግብራቸው ምስክር የሆነላቸው መሪ ድርጅቶች አሉን። መርዳት እነሱን ነው። መርዳት የእነ አሰፋ ማሩን፣ የእነ ተስፋዬ ታደሰን፣ የእነ ጸጋዬ (ደብተራውን)፣ የእነ አበራሽ፣ የእነ ሽብሬ ደሳለኝን፣ የእነ ብርቱካንን እና የሌሎችንም ወያኔን በተግባራቸው የተፋለሙ/የሚፋለሙ ሰዎች ቤተሰቦች ነው። ወያኔን በወያኔ ለመተካት እንርዳ ብለው ወደ መጎንበሱና እራስን ማዋረዱ ሊመሩን የሚሞክሩትን በቃችሁ ልንላቸው ይገባል።